በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

"ሰው አፍልጉኝ"

ተዋንያን:-

አለሙ :አለሚቱ:ትዕግስት:ማን ደፍሮ:ተራኪ:ከበደ እና አባት ናቸው::

ትዕይንት አንድ

ትዕይንቱ ሲጀምር /አሳዛኝ ክላሲካል ይሰማል/

ተራኪ:-/በመጋረጃ ውስጥ/ንጉሥ ዳዊት ልጁ ሰሎሞን" ልጄ ሆይ ሰው ሁን "ጀኛ ነገ፪:፪ ብሎታል በተፈጥሮው ሰው አልሆን ብሎ አይደለም::ሰው የተፈጠረው እንደ መላእክት ፈጣሪውን ቅዱስ ቅዱስ እያለ ሊያመሰግን ነበር::ነገር ግን ነጻ ፍቃዱን ተጠቅሞ ሁሉም የሰው ልጅ ከሰውነት ባህርይ ወጥቶ እንስሳዊ ባህርይ ገንዘብ አደረገ::ማን ሰውነቱን ይወቅ ይረዳ ማንስ ሰው ሆኖ ይገኝ? የሰማዮንገንዘብ ለመቀበል አላማ አድርጎ የሚጓዝ ሰው ጠፋ::እንዴት የሰው ልጅ ከእንስሳት ያንሳል ገብረ ጉንዳንን ማን ያስተውላት የእርሷን ጥበብ የሚያስተውል ጠፍ!

/ በሚያሳዝን አነጋገር / "ሰው አፋልጉኝ የተሰጠውን የእግዚአብሔርን ልጅነት አውቆ የተከፈለለትን ውለታ የሚያስታውስና ያንን ውለታ በተግባር ሕይወት የሚኖር ፈሪሀ እግዚአብሔር ያለው ሰው የቅዱሳንን ምልጃ ገንዘብ ያደረገ ምግባርን ከሀይማኖት አስተባብሮ የያዘ እባካችሁ ፈልጉልኝ ልቅሶየንም አቅሉልኝ አደራችሁን ወልጄ የወላድ መካን ሆኛለሁና "

ትዕይንት ሁለት

መጋረጃ ሲከፈት አባ አዝነው ተቀሚጠው ይታያሉ

አባ:-/ጥቁር ልብስ ለብሰው /ወይኔ ወዮታ አለብኝ(እያለቀሱ) የተሰጠኝን አደራ በልሁ ኋላ ከክርስቶስ ፊት ለፍርድ ስቀርብ ምን እመልሳለሁ ነፍሴ ሆይ አሁን በተሰጠሽ ስዓት ብትጠቀሚበት አይሻልሽም አሁን እየሰራሽው ያለሽው ስራ ማንን የሚያስደስት ነው እግዚአብሔር ነው ወይስ ሰይጣንን ነው? ሰይጣንን በማስደሰት የሚታገኝው ጥቅም ምንድን ነው? ኋላስ ከሳሽሽ እርሱው አይደለምን?-----አሁንም ቢሆን በአለሽ ጊዜ እግዚአብሔር አስደስች ሰው መሆንሽንም ተረጅ እና እወቂበት።

ደግሞም ካህን ነኝ የተሰጠውትን ስልጣን ካልተጠቀምኩበት ሰማያዊ እዳ አለብኝ! ወይኔ ለብዙዎች መጥፍት ተጠያቂ ነኝ የጠፉትን እፈልግ የተሰበረውን እጠግን ዘንድ እዳ አለብኝ ------- አምላኬ ሆይ መንገድህን አሳየኝ ምራኝ አሁንኑ ሰውን ፍለጋ እወጣለሁና በመንገዴ ሁሉ ተከተለኝ ደግፈኝ (ወጥተው ይሄዱሉ)

ትዕይንት ሦስት

(አለሚቱና አለሙ በአንድ ለይ ተቀምጠው ይታያሉ)

አለሚቱ:-አለሙ እንዳንተና እንደኔ ያለ እኮ ሰው በዚህች ዓለም ቢገኝ እኮ ሁሉ ነገር ያማረና የተሳካ ንሮ ሁሉም ሰው በኖር ነበር።

አለሙ:-እውነትሽን ነው በተለይ እንደ አንች ሁሉም ደግ ቢሆን ----- በዚያ ለይ ቁመናሽ ያምራል የአንች ውበት እኮ ምግብ ማለት ነው ቢመገቡት ከምግብ በላይም ነው----ደግሞ ከአንች በለይ ሰውስ ማን አለ ሰው ማለት አንች ብቻ/እራሱን እየነቀነቀ/

አለሚቱ:-እውነት ነው /ተነስታ እየተንቀሳቀሰች/---በእኔ ቁንጅና ያልተማረከ ማን አለ? ማንስ ስለ እኔ ያልሰገደ አለ? አምላክ እኮ ነው የመሰልኳቸው። ስለዚህ በዚህ ቁንጅናየ ከአሁኑኑ ስዓት ጀምሬ ልጠቀምበት ይገባኛል።ሥጋዬን እየሸጥኩ ለእኔም ሆነ ለአንተ ችግር የሚባል ነገር ድራሹን ማጥፋት አለብን አለምየ(በማቆላመጥ)

አለሙ:-ልክ ነሽ እኔም በዕየለቱ ወደ አንች እንዲመጡ አንችም ቢዝነስ ትሰሪያለሽ ለእኔም የስራ መስክ ይሆነኛል።ከዚህ በለይ ሰውነት ምን አለ?

አለሚቱ:-እሽ በል አሁንኑ ወደ ስራ እንግባ(ተያይዘው ይወጣሉ)

ትዕይንት አራት

መጋረጃ ሲከፈት ማንደፍሮ እየተንቀሳቀሰ እየተንጎራደደ ይታያል

ማን ደፍሮ:-ከእኔ በለይ ሰው መሆን ለሀሳር ነው።እኔ የፈለኩትን የማድረግ ስልጣን አለኝ በእኔ ለይ ማንም ስልጣን የለውም በጉልበቴ የሀታምችን ገንዘብ እየቀመው እጠቀማለሁ ማን ሊቃወመኝ ይችላል።ሰው መሆኑን ጠልቷል ከእኔ ጋር ጠብ ጥላቻ /እእ እእ/ የምፈልገውን የሚያስፈልገኝን ሁሉ አደርጋለሁ መንግስትም ቢሆን በእኔ ለይ ምንም ስልጣን የለውም። የምፈልጋትን ባለ ትዳርም ብትሆን ባሏን ገድየ የእኔ ማድረግ እችላለሁ ማን ሊናገረኝ።ለሁሉም አቅሜን አሳየዋለሁ ማንም አይናገረኝም ከእኔ በለይ ሰው ማን አለ? (ወጥቶ ይሄዳል)

ትዕይንት አምስት

(መጋረጃ ሲከፈት ከበደ ቦርሳ ይዞ እየተንቀሳቀሰ ይታያል)

ከበደ:-እኔ ከበደ የዚህ ዓለም ሞገሷ የሆንኩኝ የስንት ሰዎች ሕይወት በእኔ እጅ እንደሆነ ሁሉም ያውቃል። የእኔን እጅ እያዩ የሚኖሩ ስዎች ቁጥር ህዝብ ይቁጠራቸው።በአለኘ ገንዘብ ይህችን ዓለም ቀጥቅጬ የምገዛው ከእኔ በለይ ሰው ማን አለ?በገንዘቤ የፈለኩትን ሚስቶች እቁባቶች የመያዝ አቅም አለኝ። በህንጻ ለይ ህንጻ በቤት ለይ ቤት ገንብቻለሁ ብዙ መኪናዎች አሉኝ። የእኔ ቢጨዎች የእኔን እጅ እያዩ አምላክ እሰከምመስላቸው ድረስ ሲስግዱልኝ ያለው ግርማ ሞገስ ከዚህ በለይ ሰው መሆን ምን አለ?/መጋረጃ ይዘጋል/

ትዕይንት ስድስት

መጋረጃ ሲከፈት ትዕግስት ስትገባ ትታያለች

ትዕግስት :-አምላኬ ሆይ ሰው እሆን ዘንድ እርዳኝ የተፈጠርኩበትን ዓላማ ዘንግቼ ከሰውነት ባሕርይ ወጥቻለሁና። አቤቱ እንደቸርነቱ የንስሀ መንገድን ምራኝ አሳየኝ አንተ ይቅርባይ መሀሪ ነህና ይቅር በለኝ /በማልቀስ/አቤቱ ፋያታዊ ዘየማንን በመንግስትህ ያሰብክበት አምላክ ሆይ እኛንም በቸርነትህ አስበን የንስሀ እድሜ ስጠን።እመቤታችን ሆይ ወደ መሀሪው ይቅር ባይ ወደ ሆነው ልጅሽ ለምኝልን የምህረት ደጁን ይከፍትልን ዘንድ ዕለት ዕለት ምልጃሽ አይለየን። እመቤታችን ሆይ ልጅሽ ስለ እኛ የተቀበለውን ስደት ረሀብ እንግልት መከራ መስቀሉን ሞቱን እያሰብን እንድንኖር ይረዳን ዘንድ በንስሐ ታጥበን እንደቸርነቱ ክብር ደሙን ቅዱስ ሥጋውን እንቀበል ዘንድ ለምንልን።

ትዕይንት ሰባት

(መጋረጃ ሲከፈት አባ እየገቡ ይታያሉ)

አባት:-አቤቱ ጌታ ሆይ ልጆችህን ፍለጋ ተንከራተትኩ ለአገኛቸው ግን አልቻልኩም አሁንም በትዕግስት እሰከ አገኛቸው ድረስ መድከሜን አላቋርጥም አሁን ትንሽ ልረፍና ጉዞዬን እጀምራለሁ(ይቀመጣሉ) (ትዕግስት ትገባለች)

ትዕግስት:-እስከ ዛሬ ድረስ ክርስቶስ አንድነት ተለይቼ ኖርኩኝ። በኃጢአት የኖርኩበትን ዘመን ሳስታውሰው አዕምሮዬ ይስታል። አምላክ ሆይ ይህን ያህል ለእኔ ያለህ ትዕግስት ምን ያህል የበዛ ነው። አሁን አባቶችን ፍለጋ እሄዳለሁ አባቶችን የሰጠኸን አምላክ ሆይ ተመስገን -----ተመስገን (ትጓዛለች)---አባት አየሁ መሰለኝ ጌታ ሆይ ኃጢአተኛ ልጅህን እንዴት እንደምትወደኝ አውቃለሁ ተመስገን---አባ

አባት:-አቤት ልጄ ምን ሆነሽ ነው ከእኔ ምን ፈልገሽ ነው? ትዕግስት:-አባቴ እኔ ሰው አይደለሁም እና ሰው እሆን ዘንድ ይርዱኝ አባቴ እሰከ አሁን በኃጢአት ዓለም ስባዝን እግዚአብሔር አሳዝኛለሁና መንገዱን ያሳዩኝ አባቴ

አባት:-አይ ልጄ አንች ትልቅ ሰው ነሽ አሁን የጠፍ እኮ እራሱን የሚያይ ሰው ነው እራሱን የሚያይ ሰው ሁል ጊዜ የሚያስብ የሰማያዊውን ነገር ነው የእግዚአብሔርን መንግስት የምትወረስበትን መንገድ ይፈልጋል። እና ይህን መንገድ ፈልገሽ መምጣትሽ ዋጋ አለው ሁላችንም ከክርስቶስ ጋር አንድነት እንዲኖረን እኔም አንችም ዕለት ዕለት ንስሓ እየገባን የክርስቶስን ክብር ሥጋና ቅዱስ ደሙን እንቀበላለን። ከዚያ በኋላ አዲስ ሰው እንሆናለን።

ትዕግስት:-እሽ አባ

አባት:-አሁን በስም ክርስቲያን ሆነው የሚኖሩ አሉና እኔና አንች እነሱን ፍለጋ እንጓዛለን እዳ አለብንና እዳችንን ማቅለል ይኖርብናል ኋላ እንዳይፈረድብን።

ትዕግስት:-እሽ አባቴ በጸሎት ያስቡን እንጂ እከተለወታለው እርስዎ ይምሩን አልለየወትም።(ተያይዘው ይወጣሉ)

ትዕይንት ስምንት

(መጋረጃ ሲከፈት አለሙና አለሚቱ እየገብ ይታያለ)

አለምቱ:- አሁን ሀብታም ሆኛለሁ በዚህ ዓለም ዘነጥኩባት በቁንጅናየ ስንቱን ሰው አሰገድኩት ከዚህ ብሉይ ሰውነት ምን አለ?

አለሙ:-እውነት ነው አንችን የመሰለ ታላቅ ሰው በእውነት በዚህች ምድር የለም የቆንጆዎች ንግስት እኮ ነሽ። በአንች ንግስትነት እኔ ደግሞ ወታደርሽ ሆኛለሁ ስለዚህ አሁንም ቢሆን በዚህ ስራሽ ልትቀጥይበት ይገባል። እኔም መንገዱን ሁሉ አመቻቻለሁ ከዚህ የበለጠም እንቨስተር ትሆኛለሽ አሁንንው ወደማንታወቅበት ቦታ እንሂድ

አለሚቱ:-እሽ አለምየ የኔ ውድ እንሂድ(ተያይዘው ይሄዳሉ)

ትዕይንት ዘጠኝ

መጋረጃ ሲከፈት ትዕግስት እና አባ እየተጓዙ ይታያሉ

አባ:-ልጄ ትዕግስት አንችን ጨምሬ አደከምኩሽ እኔ መክሊቴን መወጣት ሲያቅተኝ አይዞሽ ምን ይባላል? እግዚአብሔር ዋጋሽን ይከፍልሻል።

ትዕግስት:-አይ አባ ለምን እንዲህ ይላሉ እኔ ወጣት ነኝ እርስዎ ደግሞ ሽማግሌ ነዎት እርስዎ ይህን ያህል ሲደክሙ በደስታ ነው የአንድ ሰው ነፍስ የሚናፍቀዎት አባት እግዚአብሔር ብርታቱን ይስጥዎት አባቴ/እየተነጋገሩ ሳለ አለሙና አለሚቱ ይገባሉ/

አለሚቱ:-ሰላም ናችሁ ሲያያችሁ የተራባችሁ የተጠማችሁ የተቸገራችሁ ትመስላላችሁ

አባ:-አዎ ተርበናል ተጠምተናል የተጠማንው ግን እናንተ እንደምታስብት የሥጋዊ ረሀብ አይደለም

አለሙ:-እንዴት?

አባ:- እኛ ስንከራተት የነበረው ድካማችን ሁሉ ቀለለልን የተራብንው የተጠማንው ሰው ነበርና ሰው አግኝተናል።

አለሚቱ:-/በመደንገጥ/ሰው ትበላላችሁ እንዴ?

አባ:-አይ ልጄ እንደሱ አንች እንደምታስቢው አይደለም "ሰው የሆነው ሰው" ፈልገን ነው

አለሙ:-(በንዴት)-----እኛ ሰው አይደለንም? አለሚቱ ደግሞ ሀብታም ናት ይህ ብቻ አይደለም እሰኪ ቁንጅነዋን ይመልከቱ ወጣቱ አረጋዊው ባለ ትዳሩ ሳይቀር በውበቷ የተማረከባት ከእርሷ በለይ ማን ሰው አለ? ለእኔም ግርማ ሞገሴ ናት!

አለሚቱ:-/ሰውነቷን እየነካካች/----እኮ ከእኔ በለይ ሰው በዚህች ዓለም የቆንጆዎች ንግስት እንደሆንኩ አታውቁም እንዴ? ስንቱን ባለ ስልጣን በዝሙት የጣልኩ ያገዳደልኩ ስንቱን ባለ ትዳር ያፍታው

የወጣቱን ስነ ልቦና የማረኩ እኔ ማን እንደሆንኩ አታውቁም -----እኮ ከእኔ በለይ ሰው ማን አለ?

አባ:-/በማዘን ስሜት/ልጆቼ የሰው ልጅ ከሌሎች ፍጥረታት ሲፈጠር ተለይቶ ፈጣሪ በእራሱ አርአያና አምሳል የፈጠረው ነው።እግዚአብሔር በባህርይው ቅዱስ ነው እኛም እርሱን መምሰል ሲገባን ለምን የእርኩሰት ስራን እንሰራለን? የተፈጠረበትን ዓላማ የሚያውቅ የጌታውን ትዕዛዝ የሚጠብቅ" ሰው የሆነ ሰው" ጠፍ።

ትዕግስት:-የተሰጠምን መክሊት የሚጠብቅ የልጅነት ድርሻውን የሚወጣ ማን ይሆን? ሁሉም በሰፊው መንገድ ተጋዙ ማን በጠባብ መንገድ ተጉዞ ሰው ይሁን? ሁላችንም የአምላክን ስጦታ በችለተኝነት በመያዛችን በጠላት ተኩላ ተወሰድን።

አለሙ:-ስለምንድን ነው የሚታወሩ?

አለሚቱ:-እኔም አልገባኝም?

አባ :-ነገሩ ግልጥ ነው ክርስቲያኖች አይደላችሁም እንዴ?

ሁለቱም በጋራ:-እንዴ ምነው ተጠራጠሩን እንዴ ማተባችን አይታየወትም(ማተባቸውን አውጥተው እያሳዩ)

አባ:-መልካም ክርስትና የፍቅር ሕይወት ነው። ክርስትና የሰላም ሕይወት ነው የፍቅር የሰላም አምላክ ክርስቶስ የመሠረተልን ነውና። እኛ ክርስቲያኖች ግን በእውነት ፍቅር በልባችን አለ? ሰላም በቤታችን አለ? ግን እሰከመቼ ድረስ በጸብና በጥላቻ እንኖራለን መቼነውስ የክርስቶስን መንገድ የምንከተል? የመንፈስ ፍሬዎችንስ ገንዘብ የምናደርጋቸው መቼ ነው? በንስሓ የምንመለሰውስ መቼ ነው? የክርስቶስ የሚስጢራቱ ተካፍይስ የምንሆነው መቼ ነው?የበይ

ተመልካች ሆነን እስከ መቼ? ክርስቶስ ብርሀን ነው እኛስ እንደ ብርሀን ልጆች የምንመላለሰው--------ብቻ ያሳዝናል(በማልቀስ)---ያች ማርያም መግደላዊትን ተመልከቻት ሰውነቷን ሁሉ በዝሙት ስታጠምድ የኖረች ነገር ግን አንድ ቀን መላ ሰውነቷን የሚያሳይ መስተዋት አዘጋጅታ ስትመለከት የለበሰችው ሥጋ አንድ ቀን አፈር እንደነሚሆን አሰበችና ሰው ትሆን ዘንድ ሰው የሚያረጋትን ክርስቶስን ፍለጋ ተንከራተተች።ክርስቶስም ኃጢአቷን ይቅር ብሎ አዲስ ሰው አደረጋት ▬▬▬▬እባካችሁ አዲስ ሰው እንሁን።

አለሙ:-እሽ ምን አድርጉ ነው የምትሉን?

አለሚቱ:-አባቴ ነፍሴን አድን ዘንድ ከመከራም አሳራፍት ዘንድ ምን ላድርግ? (ተንበርክካ በማልቀስ)

-ልጆቼ ንስሐ ገብታችሁ ክርስቶስን አስደስቱና እርሱ ደግሞ የዘለዓለም ሕይወት የሚያሰጠውን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ይሰጣችኋል እንደቸርነቱ። ክርስቶስ የሞተልን ስለ ሁላችንም ነውና የቀደመውን ክፉ ግብራችንን ትተን ራሳችንን ፍላጎታችንን ፍቃዳችንን ለእርሱ ለእግዚአብሔር እንስጠው። እርሱ ክርስቶስ እኛን ፍለጋ ተንከራተተ የነገስታት ንጉስ ሆኖ ሳለ እንደባርያ ሆነ ስለኛም ሞተልን።ስለዚህ እኛም ከቤቱ የጠፉትን ፍለጋ እንሄዳለን የእናንተ እርዳታ ያስፈልገናልና ተከተሉን

አለሚቱ:-እሽ አባ እስከ መጨረሻው ድረስ እንከተለወታለን

አለሙ:-አባ በጸሎት ያስብ ለዚህ ለተቀደሰ ዓላም አብረን በአንድነት እንጓዛለን

ትዕግስት :-አምላካችን ሆን ተመስገን ልጆችህን ሁል ጊዜ የምትጠራ ሰማያዊ ምግብን እንመገብ ዘንድ የረዳህን ተመስገን አሁን ፍለጋ እንሄዳለንና አባታችንንም አጠንክርልን

አለሙና አለሚቱ በጋራ:-አሜን(ተያይዘው ይወጣሉ)

ትዕይንት አስር

መጋረጃ ሲከፈት አለሙ አለሚቱ አባ እና ትዕግስት ሲጓዙ ይታያሉ

አባ:-ልጆቼ "ክርስትና የጥብርያዶስ ሕይወት አይደለም የቀራንዮ ጉዞ እንጂ "አዎ እራስን እንደ ሻማ እያቀለጡ ለሌላው ብርሃን መሆን ነው። ክርስቶስ በወንጌል ያለውን ታውቃላችሁ "እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ"ስለዚህ ሁላችንም ድካሙን ረሀብን ጽሙን እንግልቱን ታግሰን እንጓዛለን እግዚአብሔር ይርዳን

ትዕግስት :-እህት ወንድሞቼ እስከ መጨረሻው ልንጠና ግድ ነው ዋጋችን ከእርሱ እስከምንቀበል ድረስ "ኃይልን በሚሰጠን በክርስቶስ ሁሉን እንችላለን" እንዳለ ሐዋሪያው

(በጋራ እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው

የሚያስደነግጠን የሚያስፈራን ማን ነው)የሚለውን መዝሙር እየዘመሩ ይጓዛሉ/ማን ደፍሮ ይገባል/

ማን ደፍሮ:-እኔ ሀገር አስጨናቂው ማን ይቃወመኛል? /ድምጡን ከፍ አድርጎ በመጮህ /የስንት ጀግና የተባሉትን ስዎች ደም ያፈሰስኩ ባለ ትዳሮችን ያፈናቀልኩ ------እኮ እንደ እኔ ያለ ጀግና ማን አለ?አሁንም የቀመውት ገንዘብ አለቀ ያገኘውትን ሁሉ በቡጢ

እያልኩ ገንዘቡን እየቀመው እገድላቸዋለሁ------(--ይጓዛል-)--ከሩቅ ብዙ ስዎች እያየሁ ነው አሁን ዋጋቸውን እሰጣቸዋለሁ (በፍጥነት ይጓዛል) /እነሱ መዝሙሩን ቀጥለዋል/

ማን ደፍሮ:-አቁም ድምጣችሁን አጥፉ ያለ በለዚያ ዋጋችሁን እሰጣቸዋለሁ

አባ:-ምነው ልጄ ምን ሆንክ እንኳን ደህና መጣህ ሰንፈልግህ ነበር አሁን አንተን በማግኘታችን ሁላችንም ደስ ብሎናል (ሁሎችም ተመስገን አምላካችን ተመስገን)

ማን ደፍሮ:-(ግራ እየተጋባ) ምን ፈልጋችሁ ነው የፈለጋችሁን ማን እንደሆንኩ አታውቁም እንዴ? እኔ እኮ ማን ደፍሮ ነኝ

ትዕግስት:- ሰው ጠፍቶን እየፈለግን ነበር

ማን ደፍሮ:- እኮ ሰው ነው የፈለጋችሁ ከእኔ በለይ ሰው ማን አለ? እኔ እኮ ከሰውም በለይ ሰው ነኝ (ክንዱን ከፍ ከፍ እያደረገ) ስንቱን ጀግና ያንበረከ የጀግኖች ጀግና የእ

አባ:-ልክ ነው ልጄ ሰው መሆን አለመሆን የሚለካው በሥጋ ፍቃድ አይደለም በእግዚአብሔር በእውነተኛው ሚዛን እንጂ "በሚዛን ተመዘንክ ቀለህም ተገኘህ"እንደተባለ ከቴቄልነት ሕይወት መቼ ይሆን የምንወጣው? ደግሞ ኃይል የእግዚአብሔር እንደሆነ ልናውቅ ይገባናል "የሚመካ ቢኖር በእግዚአብሔር ይመካ" ፪ኛ ቆሮ ፲:፲፯-፲፰ እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ። ይህም ብቻ አይደለም ሰናክሪምን ተመልከተው በጉልበቱና በወታደሩ ብዛት ተመክቶ የእግዚአብሔር

ሰው የሆነውን ህዝቅያስን አጠፍለሁ ብሎ በትዕቢት ተነሳሳ።ነገር ነገር ግን ያለ እግዚአብሔር ፍቃድ የሚሆን የለምና ሰናክሪም የራሱ ወታደሮች ቸብቸቦውን ቆራርጠው ጣሉት።

ትዕግስት:-ምን ይኼ ብቻ አባ ጎልያድ በኃይሉ ተመክቶ እስራኤል ዘሥጋን አጠፍለሁ ብሎ ተነሳሳ። ልብ በአምላኩ ፍቅር የተቃጠለው ቅዱስ ዳዊት ኃይል የእግዚአብሔር እንደሆነ ያሳየው ዘንድ እግዚአብሔር መከታ አድርጎ ገጠመው ድሉም ለእግዚአብሔር ሰው ለቅዱስ ዳዊት ነበር። ስለዚህ ወንድም በራስህ መመካት አይጠቅምህም። ኃያል መሆን ትችላለህ ሥጋዊ ፍላጎትህን ድል ስታደርግ ከጠላት አሰራር ስትርቅ ያን ጊዜ በፈጣር ዘንድ ያሸናፊነትን ዋጋ ታገኛለህ።

ማን ደፍሮ:-(ለስለስ ባለ ድምጥ)------እሽ ምን አድርግ ነው የሚትሉን

አለሚቱ:-ወንድሜ እኔም እንዳንተ ካንተም በበለጠ በኃጢአት ዓለም የባከንኩ ነበርኩኝ ለስንት ሰዎች ሕይወት መጥፍት ምንክያት ነበርኩኝ አንድ ቀን ግን እግዚአብሔር ሊምረኝ ሊያስተምረኝ ሊገስጠኝ ስለፈለገ ከአባ እና ከእህቴ ትዕግስት ጋር አገናኘኝ። የቸርነት ስራውን ስለሰራልኝ አሁን አዲሰ ሰው ሆኛለሁ ልጄ ብሎ ጠርቶ "ዳግመኛ አትበድይ" አለኝ። ከእንግዲህ ከእርሱ ፍቃድ እንዳልወጣ እናቱን እየተማጠንኩ"ክርስቲያን አድርጊኝ "እላታለሁ እንደ ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ---ወንድሜ የቀደመው ክፍ ስራህ ይብቃህ!

ማን ደፍሮ:-(ወደ መሬት ተደፍቶ በማልቀስ)---አሁን ገና ገባኝ የእኔ ማንነት የሰይጣን አገልጋይ እንደነበርኩኝ ----ነፍሴ ሀይ ከአምላክሽ ፊት ስትቆም ምን ትመልሻለሽ ምን መልካም ምግባር አለሽ? ከዚያ ከማይጠፈው እሳት ማን ይታደግሻል ማንስ መከራውን ያቀልልሻል ----አሁንም ጊዜሽ ገና ነው። ይህችን ዕለት የሰጠሽ ሰው ትሆኝባት ዘንድ ነው።" የመዳን ቀን ዛሬ "እንደሆነ አወቂ ወደ ማንነትሽ ተመለሽ --------አምላኬ ሆን ደጅህን ክፈትልኝ መንገድህን አሳየኝ

አባ:-ተነሳ ልጄ እግዚአብሔር የሚፈልገው የእኛን የልባችንን መመለስ ቤታችንን እንድናስተካክል ነው። ስለዚህ ቤትህን አስተካክል የክርስቶስ ማደርያ ነውና እንዲል ኢሳያስ ፴፰÷፩

ማን ደፍሮ:-እንዴት አ ----አ --ድርጌ አባቴ

አባ:-ንስሐ ግባ ልጄ ንስሐ መመለስ ነው ወደ እግዚአብሔር አንድነት።ከእርሱ ጋር መኖር ነው።አንተ ይህን ስታደርግ እንኳን እግዚአብሔር ይቅርና በቅዱሳን መላይክት ዘንድም ታላቅ ደስታ ይሆናል። እርሱም አንዴ ከበሉት ዳግም የማያስርበውን አንዴ ከጠጡት ዳግመኛ የማያስጠመውን ሕይወት የሚሆነንንቅዱስ ሥጋውን ክብር ደሙን ይሰጥሃል።

ማን ደፍሮ :-ይህን ሁሉ ኃጢአት ሰርቼ ይቅር ይለኛል?

አባ:-ልጄ የኃጢአት ትንሽ ትልቅ የለውም እግዚአብሔር ይቅርባይ አምላክ ነው ቂም በቀል አያውቅም እርሱ እንደ ሰው አይደለምና(በጋራ ሁሎችም ተንበርክከው እጃቸውን ወደ ሰማይ ዘርግተው በጋራ (ተመስገን አምላክ ሆይ በድንቅ ሥራህ የሰበሰብከን ተመስገን)

ማንደፍሮ:-/ከወደቀበት በመነሳት/አምላኬ ሆን ማዳንህን ቸርነትህን በእኔ በደካማው ለይ አይቻለሁና አመሰግንሃለሁ /በማልቀስ/

አባ:-በሉ ልጆቼ ተቀመጡ ---/ሁሎችም ይቀመጣሉ/---ቸርነቱ በእኛ ላይ ስለበዛ ምስጋና ነው እንጂ ምን ይከፈለዋል---በሉ ቸርነቱ በእኛ ላይ ስለበዛ የምለውን መዝሙር በጋራ እንዘምር /ሁሎችም ይዘምራሉ ከበደ ይገባል/

ከበደ:- /ሽክ ብሎ ቦርሳ ይዞ ይታያል/ይህችን ዓለም እንደ ሰም አቅልጬ ገዘዋት የምፈልገውን ነገር የማድረግ ስልጣን ያለኝ እኔ ብቻ ነኝ እኮ ከእኔ በለይ ሰው ማን አለ?/ወደ አራቱም አቅጣጫ ይመለከታል/----የእኔን ኃያልነት መልካምነት የእኔን ክብር የሚመሰክሩ ሰዎችን መፈለግ አለብኝ /ይጓዛል/---ከፊት የማያቸው ሰዎች አሉ እነሱ ስለ እኔ ይመስክራሉ ገንዘብም እሰጣቸዋለሁ /ፈጠን ብሎ በመጓዝ/ ሰላም ናችሁ ምን ሆናችኃል ምን ያስጨንቃችኋል እኔ ማን እንደሆንኩ አታውቁምን? በሉ ስለ እኔ መስክሩና የምትፈልጉትን ነገር ሁሉ ታገኛላችሁ /ሁሎችም ከተቀመጡበት ይነሳሉ/

አባ:-ተመስገን አምላኬ ያለ አንተ ፍቃድ የሚሆን አንዳች ነገር የለም ተመስገን----ልጄ ልክ ነህ አንተ ማን እንደሆንክ እንመስክራለን እንናገራለን አንደበታችን የተሰጠን እውነትን እንድንናገር ነው። ሰለዚህ ልጄ አንተ እንደኛ ሰው ነህ ሰው ደግሞ ደካማ ነው ያሰበውን የፈለከውን ማድረግ አይችልም ያሰበውን የፈለገውን ማድረግና መፈጸም የሚችል አንድ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ስለ አንተ ማንነት በመመስከረም ጊዜአችንን መፈለግ ተገቢ አይደለም ላንቶስ ምን የሚረባህን ነገር አለው ከንቱ ውዳሴን መሻት ነውና ስለዚህ እውነት ስለሆነው ክርስቶስ እነግርሃለሁ። ክርስቶስ ስለ እኛ ስለ ኃጢአተኞች

መከራን ተቀበለ እኛን ጸጋን ያጎናጥፈን ዘንድ እርሱ እርቃኑን ሆነልን በሞቱ ሞትን ሻረልን ባሮች ሆነን ሳለን ልጆቼ ብሎ ጠራን ከዚህ በለይ ብዙ ነገር አደረገልን------ስለዚህ ልጄ "ስው ሁን ማንነትህን እወቅ"

ከበደ :-የምትሉት ሁሉ ነገር አልገባኝም ተከብሬ ከኖርኩበት አገር ወጥቼ ለማያውቁኝ ማንነቴን ላሳውቅ /በመናደድ እየተንቀሳቀሰ/ ---እ እ እ ጭራሽ ሰው ሁን ጭራሽ አልፈርድባቹሁም መቼ አወቃችሁኝና

ትዕግስት :-ወንድሜ አንድ ሰው ሰውነቱ የሚመዘነው የሚለካው ገንዘብ ስላለውና የሥጋ ፍላጎቱን ስላሳካ አይደለም። ቆይ ክርስቲያን አይደለህም እንዴ?

ከበደ:-/አንገቱን እየዳበሰ ምነው አይታይሽም እንዴ ተጠራጠርሽን ውዷ

ትዕግስት :-አይ ወንድሜ ክርስቲያን የሆነ ሰው በጉልበቱ በገንዘቡ በእውቀቱ አይመካም መመኪያ የሚያደርገው አንድ እግዚአብሔር ብቻ ነው ብየ ነው እና አንተም በተሰጠህ ስጦታ ልትጠቀምበት ሲገባህ የተሰጠህ ገንዘብ አንተን ሊያጠፍህ አይገባም። ክርስቶስ በወንጌል እንዲህ ብሎናልና "በሚያልፍ ገንዘብ ሰማያዊ ወዳጅ ግዙበት" እንዳለው አንተም እንዲሁ አድርግ ሰው ትሆን ዘንድ።

ከበደ:-እሽ ምን አድርግ ነው የምትሉኝ?

አባ:-ልጄ ምን ላድርግ ብሎ መጠየቅ ትልቅነት ነው። በገንዘብ ብለው የጠፉትን ተመልከታቸው። ሀናንያና ሰጲራን በራሳቸው ገንዘብ እንደጠፉ አስተውል።እነሱም ብቻ አይደሉም የነቢዩ ኤልሳዕ ደቀ

መዝሙር የነበረውን ልቡ በገንዘብ የተቃጠለውን ጊያዝን በራሱ ለይ ለምጥ ያመጣውን በ 30 ብር አምላኩን የሸጠውን ይሁዳን ተመልከት እነዚህ ሁሉ ምን ተጠቀሙ በራሳቸው ለይ ሞት አመጡ እንጂ

ከበደ:-/ወደ ምድር ተደፍቶ በማልቀስ/----እስከ አሁን ለገንዘብ የተገዘውበት ዘመን ይበቃኝል እባክዎ አባ ከዚህ ክፉ ስራ እወጣ ዘንድ ይርዱኝ

አባ:-ተነስ ልጄ እግዚአብሔር ቸርነቱን አብስቶልን ወደ ቤቱ መልሶናልና ዳግም እንዳንበድል ልንጠነቀቅ ይገባናል።ሁላችሁ በሉ ተነሱ እግዚአብሔር እናመስግን

/ይቅር ባይነህና የሚለው መዝሙር ይዘመራል/

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ከፍቅረ ሥላሴ

በደ/ነ/ገ /እማ ሸንኮሮ ሰ /ት /ቤት ኪነ ጥበባት ክፍል የተዘጋጀ

መስከረም ፳፻፲፭ ዓ.ም

